# ለኤችአይቪ/ኤይድስ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ

**የባህርይ ለውጥ ዘመቻ ማለት ምንድርነው?**

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ ማለት ሰዎች ያሉበትን ተጨባጭ ሁኔታ መረዳት፣ ከዚህም ሁኔታ በመነሳት ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው አስፈላጊ መልዕክቶች ማዘጋጀት ከዚያም የተለያዩ የመገናኛ መንገዶችን በመጠቀም ሰዎች ህይወታቸውን አደጋ ላይ እንዲጥሉ የሚያደርጓቸውን አመለካከቶች እንዲቀይሩ ማስተማር ብሎም ማሳመን የሚሉትን ሃሳቦች ያጠቃለለ ትርጓሜ አለው፡፡

ጠበብ ያለ ትርጉሙን ከወሰድን ደግሞ ይህ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ ኅብረተሰቡን ሊያስተምሩ የሚችሉ የተለያዩ የጤና ትምህርቶችን እንዲያገኝ በማድረግ ባህርይን ለአደጋ የሚያጋልጡ መንስዔዎችን መቀነስ የሚቻልበት ፈርጀብዙ ዘዴ ተብሎ ሊተረጎምም ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ የሚያተኩረው ባህርይን ሊለውጡ በሚችሉ ተግባራዊ መንገዶች ላይ ነው ማለት ነው፡፡

የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ ተግባራዊ የሆኑ መንገዶችን በመጠቀም ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በአብዛኛው እንደሚታወቀው የግለሰቦች ባሕርይ በአካባቢያቸው ባሉ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ባሕላዊ ልምዶች እንደሚቀረጹ እሙን ነው፡፡ ስለዚህም የመገናኛ መንገዶቹም እንደዚያው በማኅበራዊ ማስታወቂያዎች፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ ግላዊና ማኅበረሰባዊ መገናኛዎች፣ ወዘተ ዙሪያ ያጠነጠኑ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ኤችአይቪ የሚያመጣው አደጋና ኅብረተሰቡ ለበሽታው ያለው ተጋላጭነት እንዲቀንስ ከመደረጉ በፊት የበሽታው አደገኛ ተላላፊነት ለእያንዳንዱ ግለሰብም ሆነ ኅብረተሰብ ግንዛቤ እንዲኖረው ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ስለ ኤችአይቪ/ኤድስ መሠረታዊ እውነታዎችን በማስተማር፣ ኅብረተሰቡ የመከላከያ መንገዶችን እንዲያውቅና ተግባራዊ እንዲያደርግ እንዲሁም እነዚህን ለመጠቀም የሚረዱ መሣሪያዎችን መገልገያዎችን በማሳወቅ ሊከናወን ይችላል፡፡ ከዚህም ባሻገር የበሽታው ተጠቂዎች አካባቢያቸውን እንደ ደጋፊና አለኝታ አድርገው በመውሰድ ይህ የእነርሱ ባሕርይ ለመቅረጽ የሚያገለግል መሆኑን መገንዘብ አለባቸው፡፡

እንደሚታወቀው ኤችአይቪ በወሲብ የሚተላለፍ ኢንፌክሽን ነው፡፡ ስለዚህ በኤችአይቪ ዙሪያ የሚደረጉ ውይይቶች በሙሉ በኅብረተሰቡ መካከልም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ በወሲብና የጾታ ትምህርት እንዲሁም ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ለበሽታው ያለውን ተጋላጭነት ህዝቡ ማስተማርና ማወያየት ይገባል፡፡

ሌላው ኤችአይቪ/ኤድስ በሰዎች ላይ የባሕል ተጽዕኖ እንዲደርስባቸው የሚያደርግ በመሆኑ ይህ የባሕርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታን በመቻቻልና ለሁሉም የሚጠቅም ተስማሚ መፍትሔ በማምጣት እንዲሁም የርኅራኄ መንፈስ በሁሉም ዘንድ እንዲሰፍን በማድረግ በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ይህ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ ይህ ተላላፊ በሽታ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ በመከላከል የራሱን ተጽዕኖ በህዝቡ ላይ ለማሳደር የሚቻለውን ሁሉ ሙከራ ያደርጋል፡፡

**የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻን በብቃት ስለመጠቀም**

ብቃት ያለው የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ ከዚህ በሚከተለው መልኩ በተግባር ሊውል ይገባል፡-

- ማስተማር፡- ሰዎች ሊረዱት በሚችሉበት የፊደል ወይም የምልክት ቋንቋን በመጠቀም መሠረታዊ ስለሆነው ጉዳይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በሚደረግበት ጊዜ የዕውቀት አድማሳቸው ይሰፋል፡፡ ስለሆነም ይህ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ በሰዎች ውስጥ የባህርይ ለውጥ የማምጣትን ተነሳሽነት ሊመሰርት ይገባዋል፡፡ ይህንንም ማድረግ የሚችለው በኅብረተሰቡ ዘንድ ውይይት እንዲኖር በማበረታታት ሲሆን ይህንንም በመቀጠል መሠረታዊ ስለሆነውና ለዚህ ወረርሽኝ መከሰት ዋንኛ ስለሆኑት ምክንያቶች በአገር አቀፍ ደረጃ ውይይት እንዲኖር በማበረታታ ነው፡፡ እነዚህም ለበሽታው የሚያጋልጡ ዋንኛ ምክንያቶች፣ ሁኔታዎችና ምቹነት የሚፈጥሩ በማለት ለመከፋፈል ይቻላል፡፡ እንዲሁም ይህ የባህርይ ለውጥ ዘመቻ የመረጃና አገልግሎት ልውውጥን በተመለከተ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ኅብረተሰቡ ያለበትን አደጋ፣ ተጋላጭነትን እና የተዛባ አመለካከት ለማስወገድ ጉልህ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡
- ግንዛቤ ማስፋት፡- ይህ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ ፖሊሲ አርቃቂዎችንና መሪዎችን ስለበሽታው አስከፊነት ዕቅድ እንዲያወጡና በስፋት እንዲወያዩ ግንዛቤ በማስፋት በኩል ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ይህ ግንዛቤን የማስፋት ሂደት ከላይ ወደታች ማለትም ከብሔራዊ ደረጃ በተዋረድ እስከ ቀበሌ ድረስ ሊዘልቅ የሚችል ነው፡፡
- መድልዖንና የተዛባ አመለካከትን መቀነስ፡- የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ ከኤችአይቪ/ኤይድስ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚደረጉ መድልዖዎችንና የተዛቡ አመለካከቶችን በመቀነስ ደረጃ በኅብረተሰቡ ዘንድ ማኅበራዊ ለውጥ እንዲኖር ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡
- የእንክብካቤ አገልግሎትና ዕርዳታ ማስፋፋት፡- ይህ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎችን በመከላከል፣ እጓለማውታንና ለበሽታው አደጋ የተጋለጡ ህጻናትን በመርዳት፣ ኤችአይቪን በተመለከተ የፍላጎት ምክርና ምርምራ እንደኖር በማድረግ፣ በሽታው ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፍበትን መንገድ በመከላከል፣ ከበሽታው ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ተላላፊ በሽታዎችን በመከላከል፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ የድጋፍ አገልግሎት በመስጠት ከፍተኛ ዕርዳታ ያደርጋል፡፡

**የምንማረው ትምህርት**

ኤችአይቪ/ኤድስን ለመከላከል፣ ለተጎጂዎች ደግሞ እንክብካቤና ድጋፍ ለመስጠት ዓይነተኛው መንገድ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻን በእያንዳንዱ የፕሮግራም ዕቅድ ውስጥ ደጋፊ አካል አድርጎ ማስገባት ነው፡፡ ይህ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ የግለሰቦችን ባሕርይ ለመለወጥ በሚደረገው ተግባር ላይ ማተኮር የሚገባው

ሲሆን ግለሰቡ ለበሽታው ተጋላጭ እንዲሆን የሚያደርገውን የአካባቢያዊ ተጽዕኖንም በቸልታ እንዳይታለፍ ያሳስባል፡፡

ከዚህ አንጻር ዒላማ ተደርገው የሚወሰዱት የኅብረተሰቦች ክፍሎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በዚህ የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ ውስጥ በጉልህ እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ውጤታማ የሆኑ የተለያዩ የመገናኛ መንገዶችን መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግም አንዱ ተግባር ሆኖ መወሰድ አለበት፡፡

የፍርሃት ዘመቻን ወይም በማስፈራራት የሚደረግ ቅስቀሳን ፈጽሞ ማስወገድ ይገባል፤ ምክንያቱም በዚህ መልኩ የሚደረግ ማንኛውም ተግባር ወጤታማ አይሆንም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ የባህርይ ለውጥ ፕሮግራም በሚጀመርበት ወቅት የቁጥጥርና ክትትል ተግባራትን አብሮ መጀመሩ ለፕሮግራሙ ስኬት ጠቃሚ ስለሆነ አስቀድሞ ሊታሰብበት የሚገባ ተግባር ነው፡፡

**የባህርይ ለውጥ ግንኙነት ዘመቻ ምሳሌዎች፡-**

- በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ዕርስበርሳቸው የሚማማሩበትም መንገድ በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ማስተላለፍ፤ የምክርና ሌሎች መንገዶችንም ተግባራዊ ማድረግ፤
- የጸጉር ማስተካከያ ቤቶችንና የውበት ሳሎኖችን በማስተባበር የኤችአይቪ/ኤድስን መከላከል የሚቻልበትን መንገድ ለደንበኞቻቸው ማስተላለፍ የሚችሉበትን ሁኔታ መወጠን፣
- የአገር አቋራጭ እና በንግድ ከቦታ ወደቦታ የሚዘዋወሩ ሹፌሮች ለበሽታው ያላቸው ተጋላጭነት ከፍተኛ በመሆኑ እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከበሽታው መጠበቅ ስለሚችሉበት ሁኔታ ትምህርት ማዘጋጀት፡፡ ከሥራ ባልደረቦቻቸው የተወሰኑትን በመምረጥ የኤችአይቪ/ኤድስን መከላከል ስለሚቻልበት እና ስለኮንዶም አጠቃቀም ትምህርት እንዲሰጡ ማሰልጠን፤
- ሌሎች ጠቃሚና ለኅብረተሰቡ ገጣሚ ሆነው የሚገኙ የተለያዩ የማስተማሪያ መንገዶችን መጠቀም፡፡

ጥሥመ